## *ማነው ግዴታውን ያልተወጣው?*
## *ሕዝቡ ወይንስ ሠራዊቱ?*

*አስራ ሰባተኛው ዓመት ወያኔ ሥልጣን የያዘበት ግንቦት ግም አለ። በተለምዶ ሴኔ ግም አለ ይባል ነበር። ዘመኑ የተገላብጦሽ ሆኗል አትታዘቡኝ። መቸም ይህን ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር የሃገሬ ሰው እንጉርጉሮ ይቀናዋል። እንጉርጉሮ የአዕምሮ ወጌሻ ነው ልበል? ከሆነ እኔም ላጎራጉር፤*

*እንዲህ ያለ ዘመን፣*
*ዘመነ ጋንድያ፣*
*የሰዉ ልጅ በእግር፣*
*አህያው በአህያ።*

*ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዳር እስከ ዳር በሃገርም ውስጥ ሆነ በውጭ አገር ያሉ ሁሉ በወያኔ ተግባር እርር ድብን የማይሉ የማይቆጩ ካሉ እንደወያኔ በአህያ ላይ ተጭነው የመጡ አህዮች መሆን አለባቸው። አንባቢዎቼ በቃላት አመራረጤ አትዘከሩኝ። ጀበናን ጀበና ማለቴን ብቻ አስታውሱልኝ።*
*የወያኔ መንግሥት ሃገርን ወገንን የሚጎዳ ተግባር ይፈጽምና እዛ ላይ ትኩረት አድርገን ከመፍትሔው ሳንደርስ እኛው አናት ላይ ቦንብ ያፈነዳብናል። በቦንቡ የሞቱትን ማንቀብር የቆሰሉትን ሆስፒታል ሳናደርስ ሌላ የልጅ ልጆቻችንን የሚያጠፋ ተግባር ይፈጽማል።ይህን ድርጊት ከግንቦት* 28 ፡1983 *ዓ ም ጀምሮ እስከ ግንቦት* 28፡ 2000 *ዓ ም ስናየው ስንታዘበው ስንኖረው የቆየነው ተግባር ነው።*
*ታዲያስ ጎበዝ በአህያ ተጭነው የመጡት አላደረጉንም አህያ ብለን መናገር እንችላለን? ወይንስ ያፍዝ ያደንግዝ ተደርጎብናል? ያለበለዚያ ደግሞ በቢርቢራ እንደሰከረ አሣ በዘር ፓለቲካ ጎራ ለይተን ፍንግል ፍንግል ብለን ሕይወታችን እስከምታልፍ እንጠብቃለን? በጣም እጅግ በጣም ያሣዝናል ያስገርማል ከትግራይ እስከ ኢልባቦር ከሱዳን የሚያዋስነን መሬት ወያኔ ቆርሶ ለሱዳን ሲሰጥ ሐገሬው በሽመል ታንክ የታጠቀውን የሱዳን ሠራዊት ሲከላከል ሃገሬን አላስደፍርም በማለቱ ሲገደል ንብረቱ ተቃጥሎ በምርኮ ሲወሰድ የአየር ኃይላችን የምድር ጦራችን የፖሊስ ሠራዊታችን የት ናችሁ?*
*አዲስ አበባ ውስጥ ሐረጋዊያንን ሕፃናትን ሴቶችን ተማሪዎችን የሰባዊ መብት ተከራካሪዎችን ለመግደል? ዛሬ መሬት ገምሰው ለባዕድ የሰጡትን፤የባሕር በር ያሳጡንን፤ ወጣቱን ሠራዊት ከሱማሌያ ልከው አስከሬኑን የሚያስጎትቱትን ለመጠበቅ ከሆነ ቃልኪዳናችሁን የሃገር መጠበቁን ግዴታችሁን አልተወጣችሁም።*

*ታደለ መኩሪያ*